በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የገቢዎች ሚኒስቴር
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF REVENUES

ቀን ሐምሌ 04 2016
Date
ቁጥር 3.0/10/17
Ref.No

በአባሪው ለተዘረዘሩት በሙሉ

ባሉበት

**ጉዳዩ፡-** በአዲሱ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ 1341/2016 የተካተቱ ወይም ከቀድሞ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ 285/1994 የተደረጉ ለውጦችን ስለማሳወቅ ይሆናል፡፡

የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 ተሻሽሎ በአዋጅ ቁጥር 1341/2016 መተካቱ ይታወቃል፡፡ በዚህ መሠረት አዲሱ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከጸደቀበት ሰኔ 27 ቀን ጀምሮ የጸና እንደሚሆን ተደንግጓል፡፡ ስለሆነም በአዲሱ አዋጅ የተደነገጉ እያንዳንዳቸውን ድንጋጌዎች ተገንዝቦ መፈጸሙ እንደተጠበቀ ሆኖ ከነባሩ አዋጅ በግልጽ የተሻሻሉ ለውጦችንና አዳዲስ ድንጋጌዎችን ለማሳወቅ የተዘጋጀውን ጽሁፍ ከዚህ ደብዳቤ ጋር 14 ገጽ አባሪ ተደርጎ የተላከ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡ ሆኖም ይህ ጽሁፍ በነባሩ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ላይ የተደረጉ ለውጦችንና አዳድስ ድንጋጌዎችን ለማመላከት የተዘጋጀ እንጂ በራሱ ህግ ሆኖ የታክስ ውሳኔ ለመስጠት መነሻ ምክንያት አይደረግም፡፡

ከሠላምታ ጋር

መሰረት መስቀሌ አያና
ሚኒስትር ዴኤታ
የታክስ ኦፕሬሽን ዘርፍ

እንዲያውቁት፡-

- ለክብርት ሚኒስትር

ግልባጭ፡-

- ለሚንስትር ጽ/ቤት
- ለታክስ ስርዓት ዘርፍ
- ለታክስ ከፋዮች ምዝገባና አገልግሎት ዳይሬክቶሬት
- ለታክስ ማስታወቅ ዳይሬክቶሬት
- ለገቢ ሂሳቦች አስተዳደር ዳይሬክቶሬት
- ለታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤቶች ድጋፍና ክትትል ጽ/ቤት
- ለታክስ ዕዳ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት
- ታክስና ጉምሩክ መረጃ፣ ማብራሪያና ምክር አገልግሎት ዳይሬክቶሬት
- ለታክስ ስርዓት ማጣጣምን ክልሎች ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
  ገቢዎች ሚኒስቴር



Phone: +251 11 662 98 00/ 01/02/03/04/05/06/07/08 Fax: /+251 11 662 98 17
face book page: ministry of revenues. FBP: mor Ethiopia Twitter: erca@twitt
web site: http//www:erca.gov.et P.o. Box: 2559 Addis Ababa, Ethiopia

**በአባሪ የተዘረዘሩት፡-**

- ለከፍተኛ ግብር ከ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለመካከለኛ ግብር ከፋዮች ቁጥር 1 ቅ/ጽ/ቤት
- ለመካከለኛ ግብር ከፋዮች ቁጥር 2 ቅ/ጽ/ቤት
- ለምስራቅ አ/አ/አነስተኛ ግብር ከ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለምዕራብ አ/አ/አነስተኛ ግብር ከ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሰሜን ምዕራብ አ/አ/አነስተኛ ግብር ከ/ቅ/ጽ/ቤት

  አዲስ አበባ

- ለሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት (ሀዋሳ)
- ለባህር ዳር ቅ/ጽ/ቤት (ባህር ዳር)
- ለድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት (ድሬዳዋ)
- ለጅማ ቅ/ጽ/ቤት (ጅማ)
- ለአዳማ ቅ/ጽ/ቤት (አዳማ)
- ለኮምቦልቻ ቅ/ጽ/ቤት (ኮምቦልቻ)
- ለመቀሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት (መቀሌ)

## በአዲሱ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ 1341/2016 የተካተቱ ወይም ከቀድሞ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ 285/1994 የተደረጉ ለውጦች

### 1. መግቢያ

የተጨማሪ እሴት ታክስ በዕቃ ወይም በአገልግሎት ፍጆታ ላይ የሚጣል ታክስ ሲሆን፣ በግብአት ላይ የተከፈለን ታክስ በውጤት ላይ ከተሰበሰበ ታክስ በማቀናነስ ታክስ በታክስ ላይ እንዳይሰበሰብ ማድረግ የሚያስችል ታክስ ነው፡፡ የተጨማሪ እሴት ታክስ በደረሰኝ ላይ የተመሰረተ ዘመናዊ የታክስ ሥርዓት በመሆኑ ታክስ ከፋዮች የማቀናነሱ ሥርዓት ተጠቃሚ ለመሆን ደረሰኝ ሊኖራቸው ስለሚገባ ደረሰኝ በመጠየቅ አንዱ ሌላውን እንዲቆጣጠሩ ተደርጎ የተቀረፀ ለታክስ አስተዳደር አመቺ የሆነ የታክስ ዓይነት ነው፡፡

ከዚህም በላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ በፍጆታ ላይ የተጣለ በመሆኑ ቁጠባን የሚያበረታታ የታክስ ዓይነት ሲሆን፣ በካፒታል ዕቃዎች ላይ ተፈፃሚ ስለማይሆን ኢንቬስትመንትን የሚያበረታታ የታክስ አይነት ነው፡፡

በእነዚህ እና በሌሎችም ምክንያቶች በአለማችን ከ170 በላይ የሆኑ አገሮች የተጨማሪ እሴት ታክስን ስራ ላይ አውለዋል፡፡ ይህም በመሆኑ ኢንቬስተሮች ሀብታቸውን ስራ ላይ ለማዋል ከአንዱ አገር ወደሌላው በሚንቀሳቀሱበት ጊዜ የተጨማሪ እሴት ታክስን ባህሪያት ጠንቅቀው ስለሚያውቁ በቀላሉ ለመግባባት ምቹ ሁኔታን የፈጠረ ሲሆን፣ የሰዎች እና የዕቃዎች እንቅስቃሴ የተሳለጠ እንዲሆን አድርጓል፡፡

በአገራችንም የተጨማሪ እሴት ታክስ **ከ1994** ጀምሮ ስራ ላይ የዋለ ሲሆን፣ በአፈፃፀም በርካታ ችግሮች ያሉ ቢሆንም ከአገር ውስጥ ቀጥተኛ ያልሆኑ ታክሶች የሚሰበሰበው ገቢ መቶኛ በየጊዜው እየጨመረ እንዲሄድ የተጨማሪ እሴት ታክስ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡

የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ከወጣ ወዲህ ለሁለት ጊዜያት ያህል መጠነኛ ማሻሻያዎች የተደረጉ ቢሆንም በኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ላይ በመደረግ ላይ ያሉ ለውጦችን ተከትሎ የተሟላ ማሻሻያ ሳይደረግበት ከ20 ዓመታት በላይ ጊዜ ያስቆጠረ በመሆኑ ጊዜውን የዋጀ ማሻሻያ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## 2. የማሻሻያው ዓላማ

የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ማሻሻያ አዋጅ የሚከተሉትን ዓላማዎች ለማስፈፀም የተዘጋጀ ነው፡፡

2.1 የተጨማሪ እሴት ታክስ ስራ ላይ ከዋለበት ጊዜ ጀምሮ በአገሪቱ የኤኮኖሚ እንቅስቃሴ ውስጥ የተደረጉ ለውጦችን ያገናዘበ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ እንዲኖር ማድረግ፤

2.2 የታክስ መርሆዎችን በተከተለ መንገድ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅን በቀላሉ መረዳት በሚያስችል አኳኋን መቅረፅ፤

2.3 በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ የሚፈፀሙ ግብይቶች ተገቢው ታክስ እንዲሰበሰብባቸው ማድረግ የሚያስችል የተጠናከረ የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት፤

2.4 ዝቅተኛ ገቢ ያለው የህብረተሰብ ክፍል የታክሱ ጫና እንዳያርፍበት የተፈቀዱ ከታክስ ነፃ የመሆን መብቶች ተጠቃሚ እንዲሆን የታቀደውን የህብረተሰብ ክፍል ብቻ እንዲመለከቱ ማድረግ፤

2.5 ከታክስ ነፃ የመሆን መብቶች በግብአት ታክስ እና በውጤት ታክስ መካከል ያለውን ሰንሰለት የጠበቁ እንዲሆኑ ማድረግ፡፡

## 3. የማሻሻያው ዋና ዋና ገፅታዎች

### 3.1 አዋጁን በቀላሉ መረዳት በሚያስችል አኳኋን መቅረፅ

በስራ ላይ ያለው የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ካሉበት ችግሮች አንዱ በአቀራረፁ ውስብስብነት ምክንያት የታክሱ ባለሥልጣን ባለሙያዎች እና ታክስ ከፋዩ ህብረተሰብ በቀላሉ ሊረዱት ያለመቻል ነው፡፡

ይህ ችግር በታክስ ከፋዮች እና በታክሱ ባለሥልጣን መካከል በግብር አከፋፈል ረገድ ለሚፈጠረው ያለመግባባት ዋንኛው መንስኤ ሆኖ በመገኘቱ የታክስ ሥርዓቱ የተሳለጠ እንዲሆን አቀራረፁን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በዚህም መሠረት:-

- አዋጁን የጉዳዮችን ምክንያታዊ ፍሰት (logical flow) በተከተለ አኳኋን የማዋቀር፤
- አዋጁ የሚከተላቸው አጠቃላይ መርሆዎች ተለይተው እንዲታዩ የማድረግ፤
- ከአጠቃላይ መርሆዎች የተለዩ ሁኔታዎችን (ለምሳሌ፤ የግብአት ታክስን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች) ራሳቸውን አስችሎ የመደንገግ፤

- ለተጨማሪ እሴት ታክስ በተመዘገቡ ሰዎች ላይ ሁሉ ተፈፃሚነት የሚኖራቸውን የአዋጁን መሰረታዊ ድንጋጌዎች በቀላሉ መረዳት በሚያስችል መንገድ የመቅረፅ፣ ስራዎች ተከናውነዋል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በታክስ አስተዳደር አዋጅ ለቃላት እና ሐረጎች የተሰጠው ትርጉም ለተጨማሪ እሴት ታክስ ጭምር የሚያገለግል በመሆኑ በታክስ አስተዳደር አዋጅ ትርጉም የተሰጣቸው ቃላት እና ሐረጎች ከትርጉም ክፍል እንዲወጡ ተደርጓል፡፡

## 3.2 <u>የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ መሠረታዊ ድንጋጌዎችን እና የአስተዳደር ድንጋጌዎችን መለየት</u>

ከጉምሩክ በስተቀር የሁሉንም የታክስ ዓይነቶች አስተዳደር የሚመራ የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 ስራ ላይ የዋለ መሆኑ ይታወቃል፡፡

በመሆኑም አብዛኛዎቹ የተጨማሪ እሴት ታክስን አስተዳደር የሚመሩ ድንጋጌዎች በታክስ አስተዳደር አዋጅ ውስጥ የተካተቱ በመሆኑ፣ ከተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ እንዲወጡ ተደርጓል፡፡

## 3.3 <u>በተጨማሪ እሴት ታክስ ደንብ ውስጥ ተካተው የነበሩ መሠረታዊ ድንጋጌዎች ወደ አዋጁ እንዲመጡ ማድረግ፤</u>

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሚሰጠው ሥልጣን መሠረት የሚያወጣው ደንብ ለአዋጁ ትክክለኛ አፈፃፀም የሚረዱ ድንጋጌዎችን ከሚይዝ በስተቀር አዳዲስ ግዴታዎችን የሚጥል ሊሆን አይገባም፡፡ በዚህም መሠረት በደንቡ ውስጥ ተካተው የነበሩ መሰረታዊ ድንጋጌዎች፣ በተለይም፤

- የማስታወቅ እና የመክፈል ግዴታ፤
- የሂሳብ መዝገብ አያያዝ፤
- የታክስ ኢንቮይስ፤
- ዴቢት/ክሬዲት ሰነድ፤

ወደ አዋጁ እንዲመጡ ተደርጓል፡፡

በኢትዮጵያ ... ሚኒስቴር መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No 1

## 3.4 የአዋጁ ተፈፃሚነት ወሰን

የተጨማሪ እሴት ታክስ በባህሪው የፍጆታ ታክስ ነው፡፡ በመሆኑም የታክሱ የመጨረሻ ከፋዮች ሸማቾች ናቸው፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ በንግድ ሥራ የተሰማሩ ነጋዴዎች የሚጠበቅባቸው ታክሱን ከሸማቹ በመሰብሰብ ለመንግሥት ገቢ እንዲያደርጉ ነው፡፡ በአለም አቀፍ ንግድ ግንኙነት ወቅት ታክሱ ያለው አፈፃፀም አገር ውስጥ ከሚቀርቡ አቅርቦቶች የተለየ ነው፡፡ በዚህም መሰረት የተጨማሪ እሴት ታክስን አጣጣል በሚመለከት ኢትዮጵያ የምትከተለው የመዳረሻ መርህን (Destination Principle) በመሆኑ ታክሱ የሚጣለው ዕቃዎቹ ጥቅም ላይ በሚውሉበት አገር ነው፡፡ በመሆኑም በአዲሱ አዋጅ መሰረት ታክሱ ተፈፃሚ የሚሆነው በኢትዮጵያ ጥቅም ላይ በሚውሉ ዕቃዎች እና አገልግሎቶች ላይ ብቻ እንጂ ወደ ውጭ አገር በሚላኩት ዕቃዎች እና አገልግሎቶች ላይ አይደለም፡፡

በዚህም መሰረት አዋጁ ተፈፃሚ የሚሆንባቸውን በዝርዝር ለይቶ ማስቀመጡ አስፈላጊ ነው፡፡ በመሆኑም አዋጁ ተፈፃሚ የሚሆነው፤

- በኢትዮጵያ የግዛት ክልል ውስጥ በሚከናወኑ ታክስ የሚከፈልባቸው የዕቃ ወይም የአገልግሎት አቅርቦቶች፣
- ታክስ የሚከፈልባቸው ወደአገር የሚገቡ ማናቸውም ዕቃዎች፤ እና
- በቀጥታ በገዢው ታክስ በሚከፈልበት ኢትዮጵያ ውስጥ ቋሚ የስራ ቦታ በሌለው ሰው ከውጭ አገር ሆኖ ኢትዮጵያ ውስጥ ላለ ሰው በሚከናወን ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ላይ ነው፡፡

ሦስተኛውን በተመለከተ አንዳንድ የአገልግሎት አቅራቢዎች ኢትዮጵያ ውስጥ ምንም አይነት የሥራ አድራሻም ሆነ የንግድ ፈቃድ ሳይኖራቸው በኢትዮጵያ ለሚገኙ የተለያዩ የመንግስት እና የግል መስሪያ ቤቶች አገልግሎቶችን ያቀርባሉ፡፡ ለምሳሌ ያክል የተለያዩ ሶፍትዌሮችን ከኦራክል፣ ማይክሮሶፍት እና ሌሎች የቴክኖሎጂ ኩባንያዎች የመንግስት እና የግል መስሪያ ቤቶች ግዥ ይፈጽማሉ፡፡ የዚህ አይነቱ አገልግሎት በኢትዮጵያ ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውል በመሆኑ ታክሱ ይመለከታቸዋል፡፡ በመሆኑም በአዲሱ አዋጅ ለታክሱ አሰባሰብ ሲባል፦

- በአንድ አመት ውስጥ ኢትዮጵያ ነዋሪ ለሆኑ ድርጅቶች የውጭ ኩባንያ የሚፈጽመው አቅርቦት ዋጋ በህግ ለምዝገባ ከተቀመጠው የገንዘብ መጠን በላይ ከሆነ አቅርቦቱ የሚፈጸምለት ኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነው ድርጅት ለተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝግቦ ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ታክሱን ቀንሶ እንዲያስቀር፤



በኢትዮጵያ ... ገቢዎች ሚኒስቴር ... ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1 ... Ethiopian ... Revenues ... N. 1

- አቅርቦቱ የሚፈጸመው የመመዝገብ ግዴታ ለሌለባቸው ሰዎች ከሆነ አቅራቢው የውጭ ኩባንያ ለታክሱ እንዲመዘገብ፤ ታክሱን ሰብስቦ ገቢ እንዲያደርግ እና የታክስ ተወካዩን እንዲያስመዘግብ ይገደዳል፡፡

## 3.5. ታክስ የሚከፈልበት ግብይት

የተጨማሪ እሴት ታክስ በግብይት ላይ የሚከፈል ታክስ እንደመሆኑ ታክሱ የተጣለበትን ግብይት በግልጽ መደንገግ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ በዚህም መሠረት ታክሱ የሚከፈለው፤

- የንግድ ባህርይ ያለው ከሆነ ለአንድ ጊዜ የሚከናወንን የሚጨምር መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ተፈፃሚ የሚሆነው በተከታታይነት ወይም በመደበኛነት በሚከናወን ግብይት ላይ መሆኑ፤
- ነዋሪ ባልሆነ የሚሰጥን አገልግሎት እንደሚጨምር፤
- የቅጥር አገልግሎትን እንደማይጨምር፤ ግልፅ ተደርጓል

ከዚህም በተጨማሪ በደንቡ አንቀጽ 4(2) በግለሰብ የሚሰጥ የመዝናኛ አገልግሎትን እንደማይጨምር የተመለከተው መሠረታዊ በመሆኑ ወደአዋጁ እንዲመጣ፤ ታክስ የሚከፈልበትን ግብይት ለመጀመር ወይም ለማቋረጥ የሚከናወን ተግባር ታክስ የሚከፈልበት ግብይት እንደሚሆን በደንቡ አንቀጽ 4(1) የተመለከተው ወደአዋጁ እንዲመጣ ፤ እንዲሁም ከታክሱ ነፃ የሆነ ግብይት ታክስ የሚከፈልበት ግብይት እንደማይባል በደንቡ አንቀጽ 4(2)(ለ) የተመለከተው ወደ አዋጁ እንዲመጣ ተደርጓል፡፡

## 3.6 ተጨማሪ እሴት ታክስ የሚጣልበት ዋጋ

የተጨማሪ እሴት ታክስን በመሰብሰብ ረገድ ዋጋ መሠረታዊ ሲሆን፤ በአፈፃፀም ላይ ግን ከፍተኛ ችግር የሚታይበት ጉዳይ ነው፡፡

"የአቅርቦት ዋጋ" የታክሱን መጠን ለመወሰን እንዲሁም ታክስ ከፋዩ የመመዝገብ ግዴታ ያለበት መሆን ያለመሆኑን ለመወሰን የሚያገለግል በመሆኑ ግልፅ የሆነ ትርጓሜ እዲሰጠው ተደርጓል፡፡

በዚህም መሠረት ዋጋ (consideration or price) የሚለው ቃል በአዋጁ የትርጉም ክፍል እንደሚከተለው ተተርጉሟል፤



በኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation N 1

- ማናቸውም ሰው  በቀጥታ ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ለአቅርቦቱ የከፈለው ወይም የሚከፍለው የገንዘብ መጠን፤
- የዕቃ አቅርቦትን በሚመለከት የዕቃው አቅርቦት ለተፈጸመበት የእቃ መያዣ የተከፈለውን ወይም የሚከፈለውን እና የዕቃው መያዣ ሲመለስ ተመላሽ የሚደረገውን ተቀማጭ ገንዘብ፤
- ለአቅርቦቱ የተከፈለው ወይም የሚከፈለው የአገልግሎት ክፍያ፣ እና
- በአቅርቦቱ ምክንያት የተከፈለው ወይም የሚከፈለው ማናቸውም ቀረጥ፣ የኤክሳይዝ ታክስ፣ ሱር ታክስ፣ የአገልግሎት ክፍያ እና ሌሎች ክፍያዎች፣

## 3.7 በገቢው የሚሰበሰብ ታክስ

የተጨማሪ እሴት ታክስ የፍጆታ ታክስ እንደመሆኑ በአገር ውስጥ ወይም ከውጭ አገር በቀረበ ዕቃ ወይም በተሰጠ አገልግሎት ላይ ተፈፃሚ መሆን አለበት፡፡ ከውጭ አገር የሚቀርብ ዕቃ በመግቢያ በሮች በጉምሩክ አማካኝነት ታክሱ የሚሰበሰብበት ሲሆን ከውጭ አገር በሚሰጥ አገልግሎት ላይ አገልግሎት ተቀባዩ ራሱ ታክሱን መክፈል ይኖርበታል፡፡

ከውጭ አገር የተሰጠ አገልግሎት የሚባለው፤

- የአገልግሎቱ አቅራቢ ለተጨማሪ እሴት ታክስ ያልተመዘገበ ከሆነ፤
- አገልግሎቱ የተሰጠው ከኢትዮጵያ ውጪ ሲሆን፤
- አገልግሎቱ ታክስ ለሚከፈልበት የስራ እንቅስቃሴ የዋለ እና ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ ያልተደረገ ሲሆን ነው፡፡

በዚህም መሠረት የአገልግሎቱ ተቀባይ የታክስ ደረሰኝ (Recipient - created tax invoice)፤ በመቁረጥ ታክሱን ለግብር አስገቢው መስሪያ ቤት ገቢ ማድረግ አለበት፡፡ በውጭ አገር የሚገኝ ዋና መስሪያ ቤት ኢትዮጵያ ውስጥ ላለ ድርጅቱ የሚሰጠው አገልግሎትም በዚሁ አንቀጽ ይሸፈናል፤

## 3.8 ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ የመሆን መብት - አጠቃላይ ማስተካከያዎች

የተጨማሪ እሴት ታክስ ከሚታይበት ጉድለት አንዱ እና ዋንኛው በርካታ ዕቃዎች እና አገልግሎቶች ከታክሱ ነፃ እንዲሆኑ መደረጋቸው ነው፡፡ በአዋጁ እና በአዋጁ ለገንዘብ ሚኒስቴር በተሰጠው ስልጣን ከታክሱ ነፃ የተደረጉ እቃዎች እና አገልግሎቶች ዋንኛ አላማ ታክሱ ዝቅተኛ ገቢ ባለው የህብረተሰብ ክፍል ላይ ሊያሳድር የሚችለውን ጫና መከላከል እና የወጪ ንግድን ማበረታታት ቢሆንም ልዩነት ሳይደረግ ሁሉም ሰው ከታክሱ ነፃ በመሆኑ ዓላማውን ስቶ ነበር፡፡



Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No 1

ከዚህም በተጨማሪ መንግሥት በታክሱ አማካኝነት ሰብስቦ ለልማት ስራ ሊያውል ይችል የነበረው ከፍተኛ ገቢ እዲያጣ ምክንያት ሆኗል፡፡

በእነዚህ ምክንያቶች ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ በማድረግ ረገድ የተሰጠውን ልዩ መብት እንደገና በመፈተሽ የሚከተሉት አጠቃላይ ማስተካከያዎች ተደርገዋል፡፡

- ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ ተደርገው ከነበሩት መካከል በቂ ምክንያት ያልተገኘላቸው ታክሱ እንዲከፈልባቸው ማድረግ፤
- በማህበራዊ ምክንያት ከታክሱ ነፃ የተደረገው ዝቅተኛ ገቢ ያለውን የህብረተሰብ ክፍል ብቻ በሚጠቅም አይነት እንዲስተካከል ማድረግ፤
- ለገንዘብ ሚኒስቴር ተሰጥቶ የነበረው ከታክስ ነፃ የማድረግ ሥልጣን በምግብ አቅርቦቶች ብቻ እንዲወሰን ማድረግ፤
- ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ የመሆን መብት በቀጥታ ጥቅም ላይ ለሚውሉ የመጨረሻ ምርቶች እንጂ ለግብአቶች (intermediate) ተፈፃሚ እንዳይሆን ማድረግ፤

## 3.9 ከታክሱ ነፃ የተደረጉ የፋይናንስ አገልግሎቶች

የፋይናንስ ተቋማት ቁጠባን በማበረታታትና ኢንቬስትመንትን በመደገፍ ረገድ ያላቸውን አስተዋፅኦ እንዲሁም በአንዳንድ የፋይናንስ ግብይቶች የተጨማሪውን እሴት መለየት አስቸጋሪ መሆኑን ከግምት ውስጥ በማስገባት በስራ ላይ ባለው የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ የፋይናንስ ተቋማት ከሚሰጧቸው አገልግሎቶች ውስጥ አብዛኛው ከታክሱ ነፃ ተደርገው ቆይተዋል፡፡

ይሁን እንጂ በፋይናንስ ተቋማት ከሚሰጡ አገልግሎቶች ውስጥ አብዛኞዎቹ የታክስ ነፃ መብቱ ከተሰጠበት አላማ ጋር የማይገናኙ በመሆኑ ከታክስ ነፃ የመሆን መብት ሊቋቋምላቸው የሚገባውን ለይቶ በመዘርዘር (positive list) ከዚያ ውጭ ያሉት ታክሱ እንዲከፈልባቸው ማድረግ የተሻለ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በዚህም መሠረት፤

- ለፋይናንስ አገልግሎት የተሰጠው ከታክስ ነፃ የመሆን መብት ተቋሙን ሳይሆን የአገልግሎቱን ባህሪ እንዲመለከት በማድረግ የተሰጠው ከታክሱ ነፃ የመሆን መብት ተፈፃሚ የሚሆነው፤



በኢትዮጵያ ዜዶች ሚኒስቴር ... ቁ.1 Ethiopian ... No 1

- ብድር ከመስጠት፣ ከመሰብሰብ፣
- ከተቀማጭ ገንዘብ (deposit)፣
- አክሲዮን፣ ቦንድ፣ ሌሎች የዋስትና ሰነዶች ከመገበያየት፣
- የኢንቬስትመንት ፈንድ ከማስተዳደር፣
- የጡረታ ፈንድ ከማቋቋም፣ ጋር የተያያዘው ብቻ እንዲሆን ተደርጓል፣

በሸሪያ ሕግ መሠረት ከሚሰጡ የፋይናንስ አገልግሎቶች ውስጥ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ተለይተው የሚዘረዘሩት ከታክሱ ነፃ እንዲሆኑ ተደርጓል፣

የፋይናንስ ተቋማት በተወሰነ ክፍያ (ኮሚሽን፣ የአገልግሎት ክፍያ (fee) የሚሰጡዋቸው አገልግሎቶች ከታክሱ ነፃ ከተደረጉት መካከል እንዳይካተቱ ተደርጓል።

## 3.10 <u>የመድን አገልግሎት</u>

የመድን አገልግሎት ልዩነት ሳይደረግበት ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ መደረጉ በቂ ምክንያት የሌለው እና ከሌሎች አገሮች ልምድም ጋር የማይጣጣም ሆኖ ተገኝቷል።

በዚህም ምክንያት በመድን ስራዎች አዋጅ በተተረጎመው መሰረት ከረዥም ጊዜ መድን ( ከህይወት እና ጤና መድን) በስተቀር ሌላ ማናቸውም አጠቃላይ የመድን ፖሊሲ ለመግዛት የሚከፈል ፕሪሚየም እና ጉዳት በሚደርስበት ጊዜ የሚከፈል ካሳ በአዋጁ መሰረት ግብይት ስለሆኑ ታክሱ እንዲከፈልባቸው ተደርጓል። የህይወት እና የጤና መድን ግን ከህብረተሰቡ ማህበራዊ ዋስትና ጋር የተያያዘ በመሆኑ ከታክሱ ነፃ እንዲሆን ተደርጓል።

አጠቃላይ መድን ታክስ የሚከፈልበት በመሆኑ የመድን ድርጅቶች ስራቸውን ለማከናወን የሚያስፈልጓቸውን ዕቃዎች እና አገልግሎቶች ግዢ በሚፈፅሙበት ጊዜ የከፈሉትን የተጨማሪ እሴት ታክስ ማቀናነስ የሚችሉበትን እድል ስለሚፈጥር ጠቀሜታ ይኖረዋል።

## 3.11 <u>በመኖሪያነት ያገለገለ ቤት</u>

የከተማ ነዋሪ የሆነው ዝቅተኛ ገቢ ያለው የህብረተሰብ ክፍል ካሉበት ችግሮች አንዱ እና ዋንኛው የመኖሪያ ቤት ችግር እንደሆነ ይታወቃል።

በመሆኑም ህብረተሰቡ ያለበትን የመኖሪያ ቤት ወጪ ጫና በመጠኑም ቢሆን ለማቃለል እንዲቻል ቢያንስ ለሁለት ዓመታት በመኖሪያነት ያገለገለ ቤት ሽያጭ እንዲሁም የመኖሪያ ቤት ኪራይ ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ ሆኖ ቆይቷል፡፡

የዚህ ዓይነቱ እገዛ አስፈላጊ እና በሌሎች አገሮችም የሚደረግ በመሆኑ በነበረበት እንዲቀጥል ተደርጓል፡፡

## 3.12 <u>የትራንስፖርት አገልግሎት</u>

የትራንስፖርት አገልግሎት ከታክሱ ነፃ እንዲሆን የተደረገው አነስተኛ ገቢ ያለው የህብረተሰብ ክፍል ለትራንስፖርት የሚያወጣው ወጪ እንዳይንር እንዲሁም በጭነት ተሽከርካሪዎች ላይ የሚከፈለው ታክስ የዕቃዎችን ዋጋ መናር እንዳያስከትል ለማድረግ ነው፡፡

ሆኖም ከህዝብ ትራንስፖርት ውጪ ለሌሎች የትራንስፖርት አገልግሎቶች የዚህ አይነቱን ድጋፍ ማድረግ ተገቢ ባለመሆኑ ለትራንስፖርት አገልግሎት የተሰጠው ከታክሱ ነፃ የመሆን መብት ባለሶስት እግርን ሳይጨምር ከስምንት መቀመጫ በታች ያላቸውን ሌሎች ተሽከርካሪዎች እንዳይመለከት ተደርጓል፡፡

## 3.13 <u>የኤሌክትሪክ እና የውሃ አገልግሎት</u>

የኤሌክትሪክ እና የውሃ አቅርቦት ከታክሱ ነፃ ተደርጎ የነበረው አነስተኛ ገቢ ያለው የህብረተሰብ ክፍል ያለበትን የወጪ ጫና ለማርገብ ሲባል ነው፡፡

ይሁን እንጂ ኤሌክትሪክ እና ውሃ በብዛት የሚጠቀመው የመክፈል አቅም ያለው የህብረተሰብ ክፍል በመሆኑ የተሰጠው መብት ይበልጥ ተጠቃሚ የሆነው ይህ የህብረተሰብ ክፍል ነው፡፡ ይህ የህብረተሰብ ክፍል ደግሞ ታክሱ የሚያስከትልበት የወጪ ጫና የሌለ በመሆኑ ድጋፉ ትርጉም ያለው አይደለም፡፡

በመሆኑም ድጋፉ ታሳቢ ያደረገውን የህብረተሰብ ክፍል ብቻ በሚጠቅም መልኩ ማስተካከያ ማድረግ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ በዚህም መሰረት ከታክሱ ነፃ የመሆኑ መብት

በኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian ... Revenues ... Documentation No 1

ተጠቃሚ የሚሆኑት የገንዘብ ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ ከሚወሰን በታች የኤሌክትሪክ እና የውሃ ፍጆታ ያላቸው እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡

### 3.14 የኤሌክትሮኒክስ ግብይት

የህብረተሰብ ግንኙነት የተሳለጠ እንዲሆን ቴክሎኖሎጂ ከፍተኛ እገዛ በማድረግ ላይ የሚገኝ ሲሆን፤ በዚህ ረገድ ሊጠቀሱ ከሚችሉት አንዱ የኤሌክትሮኒክስ ንግድ ነው፡፡

የኤሌክትሮኒክስ ንግድ የአገራችንን የንግድ ዘይቤ በማዘመን ረገድ ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው ሲሆን፤ ብቃት ያለው የመከታተያ ሥርዓት ከተበጀለት ከታክሱ የሚገኘውን ገቢ ለማሳደግ እና የታክስ ማጭበርበርን ለመከላከልም እገዛ ይኖረዋል፡፡

በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ግብይት ከሚካሄድባቸው መካከል በድረገጽ፤ በኢንተርኔት፤ በፖርታል፤ በጌትዌይ፤ በመደብር (ስቶር)፤ በገበያ ቦታ ወይም በሌላ ማናቸውም አቅራቢ ከሩቅ ሆኖ በሩቅ የሚሰጡ አገልግሎቶችን ወይም በኤሌክትሮኒክ ዘዴ የሚታዘዙ ዕቃዎችን በሌላ ሰው አማካኝነት ለሶስተኛ ሰው የሚቀርብበት በኤሌክትሮኒክ ዘዴ የሚሰራ ሌላ ተመሳሳይ የኤሊክትሮኒክስ ገበያ ይገኝበታል፡፡

በመሆኑም በእነዚህ ገበያዎች የሚከናወን ግብይት የተጨማሪ እሴት ታክስ እንዲሰበሰብበት ማድረግ የሚያስችሉ ድንጋጌዎች በአዋጁ ተካተዋል፡፡ በዚህም መሠረት የሌሎችን ምርቶች ለገበያ የሚያቀርቡ እንደ አማዞን፤ ጉግል ፕሌይ፤ **አፕል ስቶር** የመሳሰሉት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚያከናውኑትን ግብይት በሚመለከት ለተጨማሪ እሴት ታክስ መመዝገብ እንዳለባቸው፤ እነዚህ የውጭ ኩባንያዎች በኢትዮጵያ ውስጥ የባንክ ሂሳብ መክፈት ያለባቸው መሆኑን፤ ባንኩ ለኩባንያዎቹ ከሚከፍለው ሂሳብ ላይ ታክሱን ቀንሶ ማስቀረት እንዳለበት ተደንግጓል፡፡

ኩባንያዎቹ በማናቸውም ምክንያት ያልተመዘገቡ ከሆነ ከእነዚህ የውጭ ኩባንያዎች በየዓመቱ ከአንድ ሚሊዮን ብር በላይ የሚያወጣ ከሩቅ የሚሰጥ አገልግሎት የሚያገኝ ለታክሱ ያልተመዘገበ በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ሰው መመዝገብ እንዳለበት እና ታክሱን እራሱ ከሚከፍለው ገንዘብ ላይ አስልቶ መክፈል እንዳለበት የሚደነግጉ አንቀፆች ተካተዋል፡፡

በኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1

### 3.15 ታክሱን የመሰብሰብ ስልጣን

በዚህ አዋጅ የተጣለው የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚወሰነው እና የሚሰበሰበው እንደአግባብነቱ በገቢዎች ሚኒስቴር ወይም በጉምሩክ ኮሚሽን ይሆናል ፡፡ ሆኖም የገቢዎች ሚኒስቴር ስለእርሱ ሆነው የተጨማሪ እሴት ታክስን እንዲወስኑ እና እንዲሰበስቡ ለክልል እና ለከተማ አስተዳደር የገቢዎች ቢሮዎች ውክልና ሊሰጥ ይችላል በሚል በአዲሱ አዋጅ ተደንግጓል፡፡

### 3.16 የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት

የቴሌኮሚኒኬሽን አገልግሎት ለማግኘት የሚያስችሉ ካርዶችን እና ሌሎችንም አቅርቦቶች በማከፋፈል ረገድ በርካታ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚሳተፉ በመሆኑ እነዚህን ታክስ ከፍዮች መዝግቦ ታክሱን እንዲሰበስቡ ማድረግ ውስብስብ አስተዳደራዊ ችግርን ያስከትላል፡፡

በመሆኑም አስተዳደሩን ምቹ እና ቀላል ለማድረግ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት የሚሰጥ ኩባንያ ለወኪሎቹ የሚሰጠው ቅናሽ ከግምት ውስጥ ሳይገባ ታክሱን በሙሉው ዋጋ ላይ እንዲሰበስብ እና ወኪሎቹ ታክሱን ከመሰብሰብ ግዴታ ነፃ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡

ሌላው ከቴሌኮሚኒኬሽን የተጨማሪ እሴት ታክስ በመሰብሰብ ረገድ አከራካሪ የነበረው በውጭ አገር የሚሰራ የኢትዮጵያ ሲም ካርድ (የሮሚንግ ስልክ) በመጠቀም የሚገኝ አገልግሎት ታክሱ የሚከፈልበት በኢትዮጵያ ነው ወይስ ስልኩ ጥቅም ላይ በዋለበት አገር? የሚለው ጥያቄ ነበር፡፡ የአለም አቀፍ ተሞክሮን ከግምት ውስጥ በማስገባት ታክሱ የሚከፈለው በኢትዮጵያ መሆኑ ግልጽ እንዲሆን ተደርጓል፡፡

### 3.17 የቱሪዝም አገልግሎት

በቱሪስት አስተጋጅነት ስራ ላይ የተሰማሩ ባለሀብቶች (tour operators) ቱሪስቶችን በማስተናገድ ለአገሪቱ የውጭ ምንዛሪ የሚያስገኙ በመሆኑ እንደማናቸውም ኤክስፖርት ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈፃሚ እንዲደረግላቸው ከረዥም ጊዜ ጀምሮ ጥያቄ ሲያቀርቡ የነበረ በመሆኑ ለዚህ ጥያቄ ምላሽ መስጠት የሚያስችል ጥናት ተደርጓል፡፡

በኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1 Ethiopian Ministry of Revenues ... Documentation No 1

በጥናቱም የተጨማሪ እሴት ታክስ ፍጆታው የተከናወነበትን ቦታ መርህ (destination principle) የሚከተል ስለሆነ መለኪያው አገልግሎቱ የተሰጠው ለማነው? ወይም ውጭ ምንዛሪ ተገኝቶበታል ወይስ አልተገኘበትም? ሳይሆን የዕቃው ወይም የአገልግሎቱ ፍጆታ የተከናወነው የት ነው? የሚለው ነው፡፡ በመሆኑም ለቱሪስቶች አገልግሎት የሚሰጠው በኢትዮጵያ ውስጥ ስለሆነ አቅርቦቱ እንደኤክስፖርት እንዲቆጠር ማድረግ የሚያስችል ምክንያት የለም፡፡

የዘርፉ ሁለተኛው ጥያቄ ቱሪስቶች በቡድን ወደአገር መጥተው የጥቅል የቱሪዝም አገልግሎት በሚያገኙበት ጊዜ ከተከፈለው ጥቅል ገንዘብ ውስጥ አብዛኛው ለመኝታ፣ ለምግብ፣ ለትራንስፖርት ወ.ዘ.ተ. የሚውል በመሆኑ አስጎብኚዎቹ የምናገኘው ቀሪውን ሂሳብ ስለሆነ ታክሱ ሊሰላ የሚገባው በቀሪው ሂሳብ ወይም በኮሚሽኑ ላይ መሆን አለበት የሚል ነው፡፡

ከዚህ በላይ እንደተገለፀው የተጨማሪ እሴት ታክስ በአለማችን ተመራጭ የታክስ ዓይነት የሆነው ግብይቱ መቆጣጠር የሚያስችል የራሱ የሆነ ሥርዓት (inbuilt mechanism) ያለው በመሆኑ ምክንያት ነው፡፡ በመሆኑም ታክሱ በጥቅል ክፍያው ላይ ተሰብስቦ ለመኝታ፣ ለምግብ ወ.ዘ.ተ ገንዘብ ወጪ ሲደረግ የተከፈለው ታክስ ከሚቀናነስ በስተቀር ከተከፈለው ሂሳብ ላይ የማቀናነስ አሰራር ከተጨማሪ እሴት ታክስ ባህሪ ጋር የማይሄድ ስለሆነ ተቀባይነት ሊኖረው አይችልም፡፡

ይሁን እንጂ በአዋጁ አንቀጽ 74 ንኡስ አንቀጽ 7 "በዚህ አዋጅ የተደነገገው ቢኖርም በቱሪስት አስጎብኚነት የንግድ ስራ ላይ የተሰማራ የተመዘገበ ሰው ይህ አዋጅ ከፀናበት ቀን አንስቶ ለሶስት ዓመታት ያህል የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚከፍለው በአገር ውስጥ ጥቅል የቱሪዝም አገልግሎት ለመስጠት ከተቀበለው ክፍያ ላይ ለመኝታ፣ ለምግብ እና ለትራንስፖርት የሚያወጣው ወጪ ተቀንሶ በሚቀረው ሂሳብ ወይም በሚከፈለው ኮሚሽን ላይ ይሆናል፡፡" በሚል የመሸጋገሪያ ጊዜ ድንጋጌ ተቀምጦዋል፡፡

ከዚያ በኋላ ግን የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ድንጋጌዎችን እና አለምአቀፍ ተሞክሮን በተከተለ መንገድ ታክሱ በጥቅል ገቢው ላይ ተሰልቶ የማቀናነስ ሥርዓት ተፈፃሚ እንዲሆን በሚያስችል መንገድ አዋጁ ተቀርጿል፡፡

በኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues ... Documentation No 1

### 3.18 የመክፈያ ጊዜ

የግብር አከፋፈል ሥርዓታችን በቴክኖሎጂ ያልተደገፈ ስለነበር ግብር ከፋዩ በየወሩ የሰበሰበውን ታክስ ለማስታወቅ እና ለመክፈል በገቢ ሰብሳቢ መስሪያ ቤቶች ዘንድ መመላለስ ነበረበት፡፡ ይህንን ምልልስ በመቀነስ ለታክስ ከፋዮች እፎይታን ለማስገኘት ሲባል፤ በአዋጁ ማሻሻያ ታክስ የሚከፈልበት ዓመታዊ ግብይታቸው ከ70 ሚሊዮን ብር በታች የሆነ ግብር ከፋዩች የሰበሰቡትን ታክስ የሚያስታውቁት እና የሚከፍሉት በየሦስት ወሩ እንዲሆን ተደርጎ ነበር ፡፡

ይሁን እንጂ ይህ ታክስ ማስታወቅ እና መክፈል በቴክኖሎጂ የተደገፈ እንዲሆን ማድረግ የተቻለ በመሆኑ የመክፈያው የጊዜ ገደብ ሦስት ወር እንዲሆን የተደረገበት ምክንያት በአሁኑ ወቅት የማይሰራ በመሆኑ ከዚህ ቀደም ሲሠራበት እንደነበረው ሁሉም ታክስ ከፋዮች የሰበሰቡትን ታክስ በየ30 ቀኑ እንዲያስታውቁ እና እንዲከፍሉ ተደርጓል፡፡

### 3.19 ለተጨማሪ እሴት ታክስ ስለመመዝገብ

በቀደመው አዋጅ ለተጨማሪ እሴት ታክስ የመመዝገብ ግዴታ ያለባቸው ዓመታዊ ታክስ የሚከፈልበት ግብይታቸው ከብር አንድ ሚሊዮን በላይ የሆነ ታክስ ከፋዮች ነበሩ፡፡

ይሁን እንጂ የገንዘብ የመግዛት አቅም እየተዳከመ መሄዱን ከግምት ውስጥ በማስገባት ይህ የገንዘብ መጠን ወደሁለት ሚሊዮን ብር ከፍ እንዲል ተደርጓል፡፡በመሆኑም ከዚህ የገንዘብ መጠን በታች ግብይት ያላቸው ታክስ ከፋዮች የሚሰበስቡት የተርንኦቨር ታክስ ይሆናል፡፡

ታክስ ከፋዮች የተጨማሪ እሴት ታክስ የማቀናነስ ሥርዓት ተጠቃሚ ለመሆን ሲሉ ግብይታቸውን ለተጨማሪ እሴት ታክስ ከተመዘገበ ሰው ጋር ማድረግን ይመርጣሉ፡፡ በመሆኑም ያልተመዘገቡ ሰዎች ከገበያ ውጪ እንዳይሆኑ በማሰብ ከግብይታቸው 75% የሚሆነው ለተጨማሪ እሴት ታክስ ከተመዘገቡ ታክስ ከፋዩች ጋር የሆነ አነስተኛ ታክስ ከፋዮች በፈቃደኝነት እንዲመዘገቡ ሲደረግ ቆይቷል፡፡

ይሁን እንጂ ታክስ ከፋዮች 75% የሚሆነው ግብይታቸው ለተጨማሪ እሴት ታክስ ከተመዘገቡ ጋር መሆኑን ለማስረዳት ችግር ስለሚያጋጥማቸው እንዲሁም ለወደፊት ሁሉም ታክስ ከፋይ ለተጨማሪ እሴት ታክስ እንዲመዘገብ ማድረግ ስለማይቀር



... of Revenues
...entation No 1

ዓመታዊ ታክስ የሚከፈልበት ግብይታቸው ከብር አንድ ሚሊዮን በላይ የሆነ ሁሉ በፈቃደኝነት እንዲመዘገቡ ተደርጓል።

## 4. <u>ማጠቃለያ</u>

የቀረበው የተጨማሪ እሴት ታክስ ማሻሻያ ረቂቅ ከ20 ዓመታት በላይ ስራ ላይ የቆየው አዋጅ የነበሩበትን ጉድለቶች የሚያርም እና ታክስ ከፋዩ ህብረተሰብ በቀላሉ ሊረዳው እና ሊፈፅመው የሚያስችል ነው። ከዚህም በተጨማሪ ግልጽነት በጎደላቸው አንቀፆች ምክንያት በታክስ ከፋዩ እና በታክስ ሰብሳቢው መስሪያ ቤት መካከል ሲፈጠር የነበረውን ያለመግባባት በማስወገድ ምቹ የሆነ የታክስ አስተዳደር እንዲኖር ያግዛል።

በሌላ በኩል ተሻሽሎ የቀረበው አዋጅ በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ከሚፈፀሙ ግብይቶች እና ከሌሎችም ዘመናዊ የግብይት መድረኮች ታክሱን መሰብሰብ የሚያስችል በመሆኑ መንግስት ኢኮኖሚው ከሚያመነጨው ሃብት ተገቢውን ድርሻውን እንዲያገኝ ያስችላል። በተጨማሪም መብቱ ከተቋቋመለት የህብረተሰብ ክፍል አልፎ የመክፈል አቅም ያለውን ሁሉ በመጥቀም ላይ ላለው የታክስ ነፃ መብት ገደብ በማበጀት መንግሥት ተገቢውን ታክስ እንዲሰበስብ ያስችላል ።